#የንባብ_ሰባቱ_ቅመሞች!

•

1) ያለምክንያት ያንብቡ:- ለማንበብ ምክንያት አይፈልጉ። የትምና መቼም ለንባብ የተመቹ ናቸው። በምክንያት የተጀመረ ንባብ ምክንያት ሲያጣ በሰበብ ይቋጫል(ሳይነበብ ይቀራል)።

2) በጥሞና ያንብቡ:- ማንኛውንም የሚያስጨንቁ፣ የሚያሳስቡ፣ የሚበታትኑ ወይም ትኩረትን ሊያናጥቡ የሚችሉ ስሜቶችን ከንባብዎ በፊት አስወግደው ማንበብ ይጀምሩ። ንባብ ትኩረት ነው!

3) ለመረዳት እንጂ ለመጨረስ አያንብቡ:- ለመረዳት ማንበብና ለመጨረስ ማንበብ ፍፁም የተለያዩ ነጥቦች ናቸው። ሰርክ ሊያሳስብዎ ሚገባው ጥራት እንጂ ብዛት አይሁን። ለዕያንዳንዷ መጻሕፍት የማይረሳ ዕውቀትና ትዝታ ይኑርዎ!

4) ከስሜት ይራቁ:- መጻሕፍት የሥጋ ሳይሆን የአዕምሮ ስፖርት ናቸው። ስለዚህ በቅድሚያ ስለመጻሕፉ ያለዎትን ስሜት አስወግደው በምክንያታዊነት ያንብቡት።

5) መጻሕፍትን አይተቹ:- ትችት የሰዎችን ሞራል ዝቅ አድርጎ ይጎዳል። ስላነበቡት መጻሕፍት መልካም ነገር ካልታየዎት ከፋውን ነገር ለራስዎ ያስቀምጡት። ከመጻሕፉ ዘጠና ዘጠኝ ረብ የለሽ ነጥቦች ይልቅ አንዷን ቁም ነገር ለሰው ያጋሩ።

6) ለስህተት አያንብቡ:- መጻሕፍትን ሲያነቡ ስህተት ፈላጊ አይሁኑ። ስህተት መፈለግ በጣም ርካሽና ቀላል ስራ ነው፣ ትልቅ ድክመትም ጭምር ነው።

7) ደራሲዎችን ያበረታቱ:- ያለ ደራሲዎቹ ፍቃድ የማንንም የድርሰት ውጤት ፎቶ ኮፒ፣ ስካን አድርገው በሶፍት ኮፒ አይልቀቁ። የጥበብ ስራዎች የብዙ ቀኖች ድካምና ልፋት ትሩፋት በመሆናቸው ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል። ጥበበኞችን ማድነቅ ከፈለጉ በቃላት ሳይሆን ስራቸውን በተገቢው ዋጋ በመግዛት ይሁን!

መጻሕፍት ከመንጋ ለነፃ ማህበረሰብ!

#ቸር_ጊዜ!

•

#በአንተነህ

#አርብ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፳፻፲፭